# ይቆጮሃል ከርሞ

በኦነግ ተዘርቶ ፣ በሸሻ ላይ በቅሎ
ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ፣ ኢትዮጵያዊ መስሎ
ላንተ ተቆርቋሪ ፣ አዛኝ ተመስሎ
በሌለ ልዩነት ፣ አማራን ከፋፍሎ
የሸዋ የጎንደር ፣ የጎጃም የወሎ
ብሎ ሊነጥልህ ፣ ከወንድምህ ጋራ
አንተኑ መጥለፊያ ፣ ሴራ እየተሰራ
ምነው አትባንንም ፣ ምን ነካህ አማራ ።

አንቱ የተባለ ፣ በገንዘብ ሲገዛ
ምሁር አሽልቦ ፣ ሆድ አደር ሲበዛ
ጠኳት እንዳየነው ፣ እንደ ሳር ላይ ጤዛ
አገር ትበተን ወይ ፣ ትፍረስ እንደዋዛ ።

የዘር የሃይማኖት ፣ ችግር የሌለባት
ወሰን አይገድበው ፣ አንዱ አንዷን ለማግባት
እኔ ትብስ አንተ ፣ ሁሌም በመግባባት
ሺ ዘመን የኖረን ፣ አገር በመገንባት
አወቅን የሚሉ ፣ መዓት አመጡባት
ምነው ደርሰው ዛሬ ፣ ጡት ነካሽ ሆኑባት
አይተነው የማናውቅ ፣ መቅሰፍት ታዘዘባት ።

አገሬ የምትል ፣ ትልቁም ትንሹ
ያፈጠጠውን ሃቅ ፣ እውነታን ስትሸሹ
ክፉ ደግ ያዩበት ፣ ሼኩና ካህኑ
ባንድነት ያፀኗት ፣ እስላም ክርስቲያኑ
ገበሬው አባትህ ፣ ካህኑ አባትህ ፣ ያቆዩአትን ሀገር
ሊያፈርሳት ነው ዛሬ ፣ ዘበናዩ ፓስተር
በዘመን አመጣሽ ፣ የኦነጎች መንጋ
ይሄው ያገራችን ፣ መሰረት ተናጋ
አገርክን ሲያፈርሳት ፣ የባዕድ ቅጥረኛ
እንዴት ቢያስችልህ ነው ፣ እንቅልፍ የምትተኛ ።

አማራ ሁን ፣ ትግሬ ፣ ጉራጌ ፣ ኦሮሞ
ከምንጊዜም በላይ ፣ ባገርህ ጨልሞ
ገለልተኛ ሆነህ ፣ የምታይ ባርምሞ
የዛሬው ዝምታህ ፣ ይቆጭሃል ከርሞ
ንቀህ ያለፍከው ቀን ፣ አይቆይህም ቆሞ ።

ታዛቢው
July 31, 2019